# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 168 ሃምሌ 28 2003 ገጽ 1


**እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በተናጠልም ሆነ በቡድን ባመቸው መንገድ ሁሉ ተጠቅሞ ወያኔ በግብርና ቀረጥ ስም የሚያደርገውን ዝርፊያ ማወክ ይኖርበታል። በግብርና ቀረጥ ስም እየተደረገ ያለውን ዘረፋና ማዋከብ ማስቆም የሁላችንም ኃላፊነት ነው!!!**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በጀርመን አገር በኑረንበርግ ከተማ የግንቦት 7 ንቅናቄና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በጋራ የጠሩት ህዝባዊ ስብሰባ በተሳካ ሁኔታ መካሄዱ ተዘገበ

በአውሮፓ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የዘንድሮውን አመታዊ የእግር ኳስ ውድድር ባካሄዱባት ታሪካዊዋ የጀርመን ከተማ ኑረንበርግ፤ የግንቦት 7 እና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ባለፈው ቅዳሜ ሃምሌ 23 ቀን 2003 ኢ.ም የጠሩት ህዝባዊ ስብሰባ እጅግ በተሳካ ሁኔታ መካሄዱንና በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን መሳተፋቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው ከላከልን ዘገባ ለመረዳት ተችሎአል።

በኑረንበርግ ጀርመን በተካሄደው በዚህ ስብሰባ ላይ ግንቦት 7ን በመወከል የተገኙት የንቅናቄው ሊቀመንበር ዶር ብርሃኑ ነጋ ሲሆኑ ኦነግን በመወከል የተገኙት የግንባሩ ከፍተኛ ሥራ አመራር አባል አቶ ተማም ባቲ ነበሩ።

የስብሰባው የመጀመሪያ ተናጋሪ የነበሩት የኦነግ ከፍተኛ ሥራ አመራር አባል አቶ ተማም ባቲ ባደረጉት ንግግር፤ ድርጅታቸው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የትጥቅ ትግል የጀመረው በኦሮሞ ህዝብ ላይ የሚደርሰውን ብሄራዊ ጭቆና ለማስቆም ሌላ አማራጭ ስላልነበረ ነው ካሉ ቦኋላ ኦነግም ሆነ የኦሮሞ ህዝብ ጥላቸው በገዛ አገራቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ ዝቅ አድርጎት ከሚገዛው ጨቋኝ ሥርዓቶች እንጂ ደረጃው ቢለያይም እንደ ኦሮሞ ህዝብ ሥልጣን ላይ በሚፈራረቁ ሃይሎች እኩል የጭቆና ሰለባ ሆኖ ከኖረው የትኛውም ህዝብ ጋር ስላልሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኢ.ህአዴግ የሚነዛውን የፍራቻ ፕሮፓጋንዳ በመርሣትና በኦነግ ላይ ያለውን ጥርጣሬ በመተው የጋራ ችግራችንን በጋራ ለማስወገድ «በሕዝቦች እና በድርጅቶች መካከል ትብብር እንዲጎለብት መሥራት የሁላችንም ግዴታ ነው» ብለዋል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ጥምረት ለነጻነትና ለእኩልነት ከኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር ጋር በሎንዶን ከተማ አዘጋጅቶት የነበረው ስብሰባ የትብብር አስፈላጊነት ላይ ግንዛቤ ያስጨበጠ እንደሆነ ተዘገበ

የጥምረት ለነጻነትና ለእኩልነት አባል ድርጅቶች የሆኑት የአፋር ህዝቦች ፓርቲና ግንቦት 7 ንቅናቄ ከኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር ጋር በመሆን ባለፈው ዕሁድ ሃምሌ 25 ቀን በሎንዶን ከተማ ጠርቶት የነበረው ህዝባዊ ስብሰባ የሁሉም ህዝቦች ጨቋኝ የሆነውን አፋኝ የወያኔ ሥርዓት በጋራ ለመገርሰስ የትብብር አስፈላጊነት ላይ የጋራ አቋም እንዳላቸው በመግለጽ መጠናቀቁን የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከሎንዶን በላከው ዜና ገለጸ።

የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባርን በመወከል ንግግር ያደረጉት የግንባሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ ሞሃመድ ያሲን ሲሆኑ ወያኔ በህዝባችን ላይ እያደረሰ ባለው አፈናና ጭቆና ከቀደምቶቹ ጨቋኝ ሥርዓቶች ሁሉ የከፋ መሆኑን ከማስመስከሩም በላይ አናሳነቱ በፈጠረበት ስጋትና ጥርጣሬ ምክንያት የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም ሲል በሂትለር ዘመን የተፈጸመውን አይነት ጭካኔ የተሞላበት ጭፍጨፋ በዜጎች ላይ እየፈጸመ ነው በማለት የወያኔን እኩይ ተግባር አጋልጠዋል። ንግግራቸውንም በመቀጠል ዜጎች ለነጻነት የሚያደርጉትን ትግል ለመቀልበስ ሽብርን በመላው አገሪቱ ያነገሰው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአሁኑ ሰዓት አካባቢውን እያጠቃ ባለው የረሃብ አደጋ የኦጋዴን ህዝብ ምንም አይነት አለም አቀፍ እርዳታ እንዳይደርሰው በመከልከል በሚሊዮን የሚቆጠር የክልሉ ህዝብ ህይወት ለከፋ አደጋ እንዲጋለጥ አድርጎታል ብለዋል።

ወያኔ በኦጋዴን ክልል ውስጥ እያካሄደ ባለው ጦርነት በያንዳንዱ ቀን ከ30 ያላነሱ ንጹሃን ዜጎች እየገደለ ነው ያሉት የኦብነግ አመራር አባል፤ በሰቶች እህቶቻችን ላይ እየተፈጸመ ካለው አስገድዶ መድፈር ወንጀል በተጨማሪ የጥቃታቸው ሰለባ የሆኑትን የአገሩ ሰዎች ከሚታወቁበት ሰፈር 50 እና 60 ኪሜ ርቄት ተወስደው እንዲገደሉና አስከሬናቸው በጅብ እንዲበላ በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ ተሰጥቶ እየተገበረ ነው ብለዋል። ባለፈው የአውሮጳዊያን አንድ አመት ብቻ ከ20 000 ያለነሱ ዘጎች በመለስ ዜናዊ ወታደሮች በግፍ ተገድሎአል ያሉት አቶ ሞሃመድ በክልሉ እየተካሄደ ያለው ዘግናኝ ጭፍጨፋ አንድን ዘር ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ከሚደረግ ወንጀል ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው መታመኑን አስረድተዋል።

በኦብነግ እምነት የወያኔ አገዛዝ በመላው አገሪቱ እያደረሰ ያለው ሰቆቃ ሊገታ ያልቻለው በወያኔ ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ሁሉም ተከፋፍሎ ለጋራ ደህንነቱና ጥቅሙ መከበር በአንድነት መነሳት ስላልቻለ ነው የሚል እምነት እንዳለ የገለጹት የኦብነግ አመራር አባል አሁን ወቅቱ በልዩነቶቻችን ምክንያት እርስ በርስ የምንራኮትበት ሳይሆን ልዩነቶቻችንን ወደጎን ትተን በጋራ መቆምና የወያኔ አስከፊ አገዛዝ ከጫንካችን ላይ አሽቀንጠረን መጣል ያለብን ነው ብለዋል።(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በቅርቡ ሱዳን ውስጥ ከሰፈሩት የኢትዮጵያ ጦር አባላት፤ አራቱ መገደላቸውና ሰባቱ ከፋኛ መቁሰላቸው ተሰማ

ሱዳን ትሪቢዩን ቢቢሲና ሌሎችም የዜና አውታሮች እንደዘገቡት ፤ አቢየ እየተባለ በሚጠራው የሱዳን አወዛጋቢ ግዛት በተጠመደ ጸረ ሰው ፈንጂ በስፍራው በሰፈሩት የኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ አደጋን ያደረሰ ሲሆን አራት ኢትዮጵያዊያን መሞታቸው እንዲሁም ሰባት የሚሆኑት በጽኑ መቁሰላቸው ታውቁአል።

እንደ ሱዳን ትሪቢዩንና ቢቢሲ ዘገባ ሰሜንና ደቡብ ሱዳን በይገባኛል ጥያቄ በሚወዛገቡባትና በነዳጅ ሀብቷ በበለጸገችው አቢየ ግዛት ውስጥ፤ 4200 የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት አባላት በሰላም አስጠባቂነት ስም በተሰማሩ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አደጋው መድረሱ ተገልጹአል።

ከዚሁ ዘገባ ጋር ተያይዞ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ቃል አቀባይ ማርቲን ኔሲርኪ እንዳሉት፤ አቢየ ግዛት ውስጥ የሞትና መቁሰል አደጋው የደረሰው የሰሜን ሱዳን ጦር በሚንቀሳቀስበትና የደቡብ ምስራቅ አቢየ ክፍል "ማቦክ" ተብሎ በሚጠራ ቦታ ላይ ነው። በፍንዳታው ወዲያው ከሞቱት አራት የኢትዮጵያ ወታደሮች በተጨማሪ ፤ ሌሎች ሰባት ከፋኛ መቁሰላቸውንም ቃል አቀባዩ አመልክተዋል። ቁስለኞቹ፤ በደቡብ ኮርዶፋን የሱዳን ግዛት ወደምትገኘው "ካዱጂሊ" ከተማ ተወስደው ህክምና እየተደረገላቸው መሆኑንም ሚስተር ማርቲን ተናግረዋል።

ሱዳን፤ ፀረ-ሰው ፈንጂን ከመጠቀም የሚያቅበውን የኦታዋ ስምምነት የፈረመች ቢሆንም፤ የፈንጂ አደጋው የደረሰው የካርቱም መንግስት ታማኝ ወታደሮች በሚቆጣጠሩት ግዛት ውስጥ መሆኑ፤ ብዙዎችን እያነጋገረ ነው።

ቀደም ብለን ባቀረብነው ዘገባ ወደ ግዛቷ የባዕድ ጦር በመግባቱ ደስተኛ ያልሆነችው ሰሜን ሱዳን፤- "ወደ አቢየ የተንቀሳቀሰው የኢትዮጵያ ሰላም አስጠባቂ ሀይል በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ትእዛዝ ስር እንዲሆን አልፈልግም" በማለት; በተዘዋዋሪ መንገድ በኢትዮጵያ ጦር ላይ ያላትን ተቃውሞ ማስታወቁአን ገልጸን እንደነበር አይዘነጋም።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ለተመሳሳይ ተልእኮ ሶማሊያ ውስጥ በርካታ የኢትዮጵያ ወታደሮችን አስፍሮ እንደነበርና፣ በገጠመውም ሽንፈት ምክንያት ሶማሊያን ለቆ እንዲወጣ መገደዱ የሚታወስ ሲሆን ሶማሊያ ውስጥ ያለቁት የኢትዮጵያ ወታደሮች ምን ያህል እንደሆኑ እንዳልተገለጸ መዘገቡ ይታወሳል።

በሌላ በኩል ይህ የአልበሽር አስተዳደር እያሰማ ያለው ተቃውሞ ከአሁኑ አደጋ ጋር ተደምሮ ሞቅ ቀዝቀዝ ሲል ቆየውን የኢትዮጵያንና የሱዳንን ግንኙነት ዳግም ሊያደፈርሰው ይችላል የሚሉ አስተያዬቶች እየተደመጡ ነው።

## አረመኔው የወያኔ አገዛዝ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን በረሃብ አለንጋ እየተገረፉ ባሉበት ባሁኑ ሰአት ኢትዮጵያ ውስጥ ድርቅ እንጂ ረሃብ የለም አለ

ከ 14 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን በርሃብ አለንጋ እየተገረፉና በተለይም ከ 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት በአስቸኳይ ጊዜ ርዳታ ውስጥ ባሉበት ባሁኑ ሰአት ኢትዮጵያ ውስጥ ድርቅ እንጂ ረሃብ የለም፣ የተከሰተው ድርቅ በምንም ዓይነት ሁኔታ ወደ ረሃብ አይሸጋገርም በማለት የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ የሆነው ሆድ አደሩ ምትኩ ካሳ ማስታወቁን ለዘረኛው አገዛዝ ቅርበት ያለው የሪፖርተር ጋዜጣ ገለጸ::

እንደ ሪፖርተር ዘገባ ዘረኛው አገዛዝ እያደረገ ባለው ጥረት ችግሩ ከቁጥጥር ውጭ እንዳልሆነ ይሄው ባለስልጣን ተብየ መግለጹ የታወቀ ሲሆን ከሰኔ 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት በኢትዮጵያ የሚገኙ 4ነጥብ .5 ሚሊዮን ሰዎች የምግብ ዕርዳታ እንደሚፈልጉ አልካደም:: ሆድ አደሩ ሚንስትር ዴታ ምትኩ እንደተናገረው እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች በተከሰተው ድርቅ ለረሃብ እንዳይጋለጡ 398.4 ሚሊዮን ዶላር ያስፈልጋል በማለት አስገራሚና አሳዛኝ የሆነ ቃለ ምልልስ ማድረጉ ሳያንሰው «ለዕርዳታ በቀረበው ጥሪ መሠረት ዕርዳታ ሰጪዎች ሲሰጡን በጉዞ እስከ አራት ወር ሊቆይ ይችላል፤» «እኛ ከመጠባበቂያ እህል ክምችት ወጭ በማድረግ ዜጎች እንዳይራቡ እናደርጋለን:: ዕርዳታው ሲመጣም ከክምችት ያወጣነውን እንተካለን፤» ሲል መግለጹ ታውቁአል::

"በኢትዮጵያ ድርቅ ብዙውን ጊዜ የተመጣጠነ የምግብ እጥረት ይከሰት ነበር፤ አሁን ግን ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት በየቀበሌው ሁለት ሁለት የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ተመድበዋል" በማለት በህዝብ ህይወት የሚቀልደው ሚንስትር ዴታ «ሠራተኞቹ በየቤቱ እየተዘዋወሩ የሚሠሩ በመሆኑ የየቤቱ መረጃ አለን:: ከዚህ ጋር የሚነሳው ስማችን አሁን የለም፡፡ ችግሩን ፈተነዋል፤» በማለት በቅጥፈት ተናግሩአል።

ዘረኛውና አረመኔው የወያኔ አገዛዝ በአለም አቀፍ ደረጃ ይፋ የሆነ ጥሪ የተደረገለትን ይህን የርሃብ አደጋ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳልተከሰተ በማድረግ ህዝብን ለማደናገር የሚያደርገውን ሙከራ አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡት ዘጋቢያችን አንድ በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆኑ የኦጋዴን ክልል ተወላጅ በሰጡት (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛ የግብርና የቀረጥ ሥርዓትን እንቢ እንበል!!!

በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሠርቶ ማደር ወንጀል ሆኗል። ኑሮን ለማሸነፍ ደፋ ቀና እያሉ ያሉ ወጣቶች፣ ጎልማሶችና አዛውንት በግብር ሰብሳቢ ቢሮ ሹማምንት፣ ፓሊሶችና ካድሬዎች እየተዋከቡ፤ ከገቢያቸው ጋር ምንም ዓይነት ዝምድና የሌለው የግብርና ታክስ እዳ እየተቆለለባቸው መፈጠራቸውን እንዲረግሙ እየተደረገ ነው።

በምርጫ 97 ሰሞን የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ግብርን በድምጽ መግዣነት መጠቀሙ የምናስታውሰው ነው። ያኔ ማጣፊያው ያጠረ፤ ቀኑ የተቆጠረ ሲመስለው የግብር "ምህረት" በማድረግ የንግዱን ማኅበረሰብ ፍቅር ለመግዛት መሯሯጡ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ድምጽ ዘርፎ፤ ህዝብን ገድሎና አስሮ ስልጣኑ ላይ ከተደላደለ በኋላ ግን ግብርና ታክስ የምርጫ ቂሙን መበቀያ አድርጎት ነበር። አሁን ደግሞ ተቃዋሚዎች የተዳከሙ፤ እሱ ደግሞ የጠነከረ ሲመስለው መቾም ቢሆን በማይረካ ስግብግብነት እንደ አልቅት የለፍቶ አዳሪውን ዜጋ የድካም ውጤት እየመጠጠ ድሆችን ይበልጥ እያደኸየ፤ ቀድሞውኑ የደከመውን የአገራችንን ኢኮኖሚ ጭራሹን እየገደለው ነው።

የመለስ ዜናዊ ሎሌዎች በሚጠሉት ነጋዴ ላይ በጭንቅላታቸው የመጣላቸውን ትልቅ ቁጥር በግብር እዳነት መጫን ከምርጫ 97 ማግሥት ጀምሮ የተለመደ ሆኗል። በወያኔ ጥርስ የተነከሰበት ነጋዴ የሂሳብ መዝገብ ይዞ ቢቀርብ እንኳን በሰበብ አስባቡ ሂሳቡ ውድቅ ተደርጎ "የግምት" ግብር ይወሰንበታል።

ከሁሉም በላይ አሳዛኝና አሳሳቢው ጉዳይ የወያኔ የግምት ግብር ተመን መነሻው የከፋዩ ዘር የመሆኑ ሃቅ ነው። ከዘር ቀጥሎ የሚመጣው መስፈርት ደግሞ የፓለቲካ ታማኝነት ነው። የትግራዩን ገዢ ጉጅሌን በሥልጣን ላይ ለማቆየት የመሃል አገሩን ሰው በኢኮኖሚ ማዳከም እንደሚገባ መለስና ባልደረቦቹ ተነጋግረው የወሰኑት ጉዳይ ነው። ከፍ ያለ ግብርና ታክስ መጫን እና በንግድ ፈቃድ እድሳት ማጉላላት የመሃል አገሩን ሰው በኢኮኖሚ የማዳከም ፓሊሲ አካል ናቸው። በዚህም ምክንያት በርካታ ንግዶች ተዘግተውለትግራዩ ገዢ ጉጅሌ አባላትና አሽከሮቻቸው ተዛውረዋል። ይህ ሁሉ ደባ በኢትዮጵያዊያን ላይ ሲፈፀም የወያኔ ነጋዴዎች ግን የንግድ ፈቃድ ችግርም ሆነ የግብርና ታክስ ሸክም የለባቸውም። ይህንን የአፓርታይድ የንግድና ግብር ሥርዓት እስከመቼ እንታገሳለን?

በአገዛዙ ዘረኛ ዘረፋ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ለኢትዮጵያዊያን ሠርቶ የእለት ጉርስን መቻል ታላቅ ስኬት ሆኗል። የትርፍ ግብር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የጉምሩክ ቀረጥ ተቀናቃኞችን ነጥሎ ለመምታትና ድሆችን ይበልጥ ለማደህየት የተጠመዱ የመለስ ዜናዊ መሣሪያዎች ናቸው።

በተባበሩት መንግሥታት የልማት መርሃግብር (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ) መረጃ መሠረት መለስና አጫፋሪዎቹ 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር (ማለት 150 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር) ከአገር አሸሽተዋል። ህዝብ በችጋር እያለቀ፤ የዓለም ማኅበረሰብ ለነብስ አድን እርዳታ እየተሯሯጠ ባለበት ባሁኑ ወቅት አንድ መቶ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር (ማለትም 17 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር) ለታንክ ግዥ አውሏል። ብዛቱ መገመት የሚያስቸግር መጠን ያለው ሃብት ከመሬትና ማዕድናት ሽያጭ እየሰበሰበ ነው።

ይህ ሁሉ ሆኖ ግን መለስና ቡችሎቹ አይጠግቡምና በጉሊት ችርቻሮ ላይ ያሉትን እናቶችን ሳይቀር በአስር ሺህ ብሮች ግብር ክፈሉ እያሉ ነው። የንግዱ ማኅበረሰብ ምን ይሁን? አቅም ያለው አገሩን ለመለስ ዜናዊና ቡድኖቹ ትቶ በአራቱም ማዕዘናት እየተሰደደ ነው። አቅም የሌለው የት ይግባ? ደግሞስ የሚወዳትን አገሩን ለመለስ ዜናዊ እና ሽፍታ ጓደኞቹ ትቶ መሰደድ መፍትሄ ነውን? በጭራሽ። መፍትሄው መለስን መፋለም ብቻ ነው።

የመለስ አገዛዝ "ግብር" ወይም "ታክስ" ብሎ የሚጠራቸው ነገሮች እውነተኛ ስማቸው "ዝርፊያ" ነው። ንብረታችንን ከኪስ አውላቂ የመጠበቅ መብት እንዳለን ሁሉ በተቻለን መጠን ከወያኔ ንጥቂያና ዝርፊያ ራሳችንን መጠበቅ ተቀባይነት ያለው ተግባር ነው። ለወያኔ ግብርና ቀረጥ አለመክፈል የህዝብ ሃብት በወንበዴዎች እጅ እንዳይወድቅ የሚያደርግ የሚወደስ አኩሪ ተግባር ነው። ስለሆነም "ግብርም ሆነ ቀረጥ አንከፍልም" መባል ያለበት ወቅት አሁን ነው።

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በተናጠልም ሆነ በቡድን ባመቸው መንገድ ሁሉ ተጠቅሞ ወያኔ በግብርና ቀረጥ ስም የሚያደርገውን ዝርፊያ ማወክ ይኖርበታል። በግብርና ቀረጥ ስም እየተደረገ ያለውን ዘረፋና ማዋከብ ማስቆም የሁላችንም ኃላፊነት ነው!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ህዝብን ከቀየው የማፈናቀል ተግባሩን ለመቀጠል በዝግጂት ላይ መሆኑ ተገለጸ

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ቀደም ብሎ ያፈናቀላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በረሃብ አለንጋ እየተገረፉ በሚገኙበት ባሁኑ ወቀት አሁንም አዲስ የሰፈራ ፕሮግራም እንደሚጀምር ማስታወቁን ክርስቲያን ሞኒተር በመባል የሚታወቅ የዜና አውታር ገለጸ። እንደ ክርስቲያን ሞኒተር ዘገባ በተለይም በከፊል ዘላን የሆነዉን የሶማሊያ ክልል አርብቶ አደር ህዝብ ቋሚ በሆኑ መንደሮች የማስፍር ስራ በቅርብ ቀን እንደሚጀምር ዘግቧል።

ቀደም ብሎ በ1980ዎቹ የረሃብ አደጋ ወቅት የኮሎኔል መንግስቱ ሃ/ማርያም ማርክሲስት ወታደራዊ አገዛዝ በርካታ የደጋ ሰዎችን ለም ወደሆኑ ዝቅተኛ ስፍራዎች ያለ ፈቃዳቸዉ በሃይል እንዳሰፈረ ጋዜጣዉ በመግለፅ በአሁኑ ወቅት የሚደረገዉ ሰፈራ በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተና በጅምላ ሳይሆን ክልልን በተመረኮዘ ሁኔታ እንደሚከናወን ከአገዛዙ ባለስልጣናት እንደተገለጸለት አስታዉቋል። ይሁን እንጂ ዘረኛው አገዛዝ ቀደም ብሎ ያከናዎናቸው ህዝብን ከቀየ የማፈናቀል ተግባራት በግዴታ የተፈጸሙና ውጤታማ ያልሆኑ አሁንም በተመሳሳይ መልኩ የሰፈራ ፕሮግራሙ በግዴታ እንደሚሆን የውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ።

ዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ቀደም ብሎ በጋምቤላ አካባቢ የሚገኙ በመቶ ሺሆች የሚቆተሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በግዴታ ከቀያቸው በማፈናቀል በሰፍራ ስም ካአካባቢያቸው ማስወገዱና ዚጎቹም የለቀቁትን ሰፋፊ ለም መሬት ለውጪ ሃገራት ባለሃብቶ እጅግ ርካሽ በሆነ ዋጋ በመቸብቸብ ኢሰብአዊ ድርጊትን ሲፈጽም መቆየቱ ይታወሳል።

## በፍትህ ሚኒስቴር ኢሃዴግን በአባልነት አለመቀላቀል፣ የጥብቅና ፈቅድ ከማግኘት እንደሚያስከለክልና ሌላ ስራም ለመቀጠር እንደማያስችል ታወቀ

በፍትህ ሚኒስቴር ኢሃዴግን በአባልነት ያልተቀላቀለም ሆነ ለመቀላቀል ፈቃደኛ ያልሆነ የህግ ባለሙያ፣ የጥብቅና ፈቅድ ማግኘት እንደማይችልና ሌላ ስራም ለመቀጠር እንደማማይፈቀድለት የውስጥ ምንጮቹን ዋቢ በማድረግ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈው ሪፖርት ገለጸ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በፍትህ ሚንስቴር ከፍተኛ አመራር አካላት ከመነጨ የውስጥ ሚስጥር በሚኒስትሩ የማናጅመንት አባላት ተወስኖ ተግባራዊ ከሆኑት መመሪያዎች አንዱ የመስሩያ ቤቱ የህግ ባለሙያዎች ኢህአዴግን በአባልነት መቀላቀል እንደሆነ ታውቋአል። በመመሪያው መሰረትም ወያኔ ኢሃዴግን እንዲቀላቀሉ ተጠይቀው በተለያዩ ምክንያቶች ፈቃደኛ ያልሆኑ የህግ ባለሙያዎች በመስሪያ ቤቱ ማናጅመንት ውሳኔ የጥብቅና ፍቃድ እንዳያወጡ እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን ስራዎች እንዳይቀጠሩ በውሳኔ ታግደዋል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ከጥቂት አመታት በፊት በጥቂት ሺሆች ይቆጠሩ የነበሩ አባሎቹን ቁጥር ከአምስት ሚሊዮን በላይ እንዳሳደገ የሚታወቅ ሲሆን፣ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የወያኔ ኢህአዴግ አባል የሚሆኑ ግለሰቦች በግዴታ፣ በጥቅማጥቅምና፣ አጣብቂኝ ውስጥ በመግባታቸው እንደሆነና ለወያኔው ኢህ አዴግ አገዛዝ ምንም አይነት ፍላጎትም ሆነ ድጋፍ የሌላቸው መሆናቸውን መዘገባችን ይታወሳል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሰሜን ሸዋ የሚገኙ መምህራን ለወያኔ ኢሃዴግ የአባልነት ክፍያ አንከፍልም በማለት ቆራጥ ርምጃ መውሰዳቸውን መዘገባችን አይዘነጋም።

## የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ገደብ የለሽ መሬት ችብቸባ የረሃብተኛውን ቁጥር እንዲጨምር እያደረገ ነው ተባለ

ኤ ኤፍ ፒ በመባል የሚታወቀው የዜና አውታር ባወጣው ጽሁፍ ኢትዮጵያ ውስጥ እጅግ ሰፋፊ የሆኑ ለም መሬቶች ለውጪ ሃገራት ኢንቨስተሮች በርካሽ ዋጋ መሸጣቸው በአሁኑ ሰአት በቀጥታ በርሃብ አለንጋ እየተገረፉ ባሉት በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ቁጥር ላይ ተጨማሪ ሸክም እየሆነ መምጣቱን ዘግቡአል።

ኤ ኤፍ ፒ አሜሪካ ውስጥ የሚገኘውን ኦክላንድ ኢንስቲትዩት በመጥቀስ ባወጣው ዘገባ እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ከ 2008 ወዲህ ባለው ጊዜ ለሽያጭ ከዋልው ለም መሬት ውስጥ ከ350 ሺህ ሄክታር በላይ ከሚሆነው የምእራብ ኢትዮጵያ ለም መሬት የተፈናቀሉ ከ 200 ሺህ በላይ ኢትዮጵያዊያን ለረሃብ አደጋ ተጋልጠው እንደሚገኙ በዚሁ ጽሁፉ ላይ አጋልጡአል። የኦክላንድ ፖሊሲ ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ፍሬደሪክ ሙሴዩ እንደተናገሩት ዜጎችን ከለም መሬታቸው በማፈናቀል ለርሃብ እንዲዳረጉ ማድረግ ተቀባይነት የሌለውና ሊታመንም የማይችል፣ እየተሰራ ነው የሚባለውም ልማት ለዜጎቹ ጠቀሜታን የማይሰጥ ነው ብለዋል። ሙሴዩ አክለውም ባሁኑ ሰአትም ከዘጠና ሺህ ሄክታር በላይ ለም መሬት ለባለሃብቶች ተሸጦ በቦታው የሚገኙትን ዜጎች ለማፈናቀል ዝግጁ ነው ይህም በርካታ ትውልዶች ለረጅም ጊዚያት ይዘው ኑሮአቸውን ይገፉበት የነበረውን ቀየ አስለቅቆ ወደ ረሃብተኝነት ጎራ እንዲቀላቀሉ ማድረግ በጣም አሳዛኝ ተግባር ነው ብለዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአለማችን በተከሰተው የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በርካታ ሃገራት ህዝቦቻቸውን ለመመገብ በቂ እህል ማምረት ባለመቻላቸው ፊታቸውን ወደ ድሃ ሃገራት በማዞር፣ እጅግ ሰፋፊና ለም መሬቶችን በርካሽ ዋጋ እየገዙ እንደሚገኙ ዘጋቢው አክሎ ገልጹአል።

በሌላም በኩል ከእንግሊዝ፣ ከቻይና፣ ከገልፍ ስቴቶች፣ ከሳኡዲ አረቢያ፣ እንዲሁም ከደቡብ ኮሪያ የተጉአዙ ባለሃብቶች እንደኢትዮጵያ ካሉ ሃገራት እያደረጉት ያለው ገደብ የለሽ የመሬት ቅርምት ለረሃብተኞች ቁጥር መጨመር አስተዋጽኦ እንደሚያደርግና አሁን እየታየ ላለው ረሃብ አንዱ መንስኤ ይሄው የመሬት ሽያጭ ነው ብለው እንደሚያምኑ የጀርመን ሃገር የአፍሪካ ጉዳዮች አስተባባሪ ጉወንተር ኑኬ መግለጻቸውን የዘገባ ምንጩ አክሎ ገልጹአል።

ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪቃ ባሁኑ ወቅት እየታየ ካለው የርሃብ አደጋ ተጎጂ ከሆነው ህዝብ ቁጥር አብዛኛውን ድርሻ የያዘች ሲሆን፣ በርሃብ አለንጋ እየተገረፈ ያለው የህብረስተሰብ ክፍልም ከ 12 ሚሊዮን በላይ እንደሆነ ይታወቃል። ከዚህ ቁጥር ውስጥ ከ 4.5 ሚሊየን በላይ የሚሆነው በአስቸኩአይ ጊዜ ርዳታ ስር የሚገኝ ነው። ኤ ኤፍ ፒ ባውጣው ዘገባ ኢትዮጵያዊያን አርሶ አደሮችና ዘላኖች በሰላም ከሚኖሩባቸው ቀያቸው ያለፈቃዳቸው ወደ ሌላ ቦታ በግዴታ ወስዶ ማስፈር ህገ መንግስቱ የሚከለክል መሆኑ እየታወቀ የኢትዮጵያው አገዛዝ ግን ከዚህ ተቃራኒ የሆነውን አከናውኑአል ብሉአል።

እውነታው ይህ መሆኑ በስፋት እየታየና እየታወቀ የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ባለሟል በረከት ስምኦን በኢትዮጵያ እየታየ ያለው የመሬት ሽያጭ በዘገባው ላይ እንደተገለጸው ህዝብን ለርሃብ የዳረገ ሳይሆን ታስቦበትና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተሰራ ነው በማለት ነጭ ውሸት መዋሸቱ የ ኤ ኤፍ ፒ ዘጋቢን ማስገረሙ በዚሁ ዘገባ ላይ ተገልጹአል።

# “ወይን ለመኖር” የት ያደርሰናል?

ርዕሰ አንቀጽ ቁጥር 76 ጥቅምት 19 2002 ዓ.ም ወጥቶ የነበረና አሁን በድጋሜ የቀረበ

ለመኖር ብሎ የወያኔ አባልነት ፎርም መሙላት “ወይን ለመኖር” የሚል ስያሜ አግኝቷል። ስታሊናዊ ሁሉን ጠቅላይ አገዛዝ፤ “እንድዘርፍ አግዘኝ፤ አለበዚያ አጠፋሃለሁ” ዓይነቱ የማፍያ አሠራርና እና ግብር በማብላት የመኮፈስ ፊውዳላዊ ባህል ሲዳቀሉ “ወይን ለመኖርን” ፈጠሩ። “ወይን ለመኖር” ያልተፃፈ ነገር ግን ከተፃፈው በላይ እየተገበረ ያለ የወያኔ ህገ-መንግሥት ነው። ስለሆነም “ከወይን ለመኖር” ጋር የማይጣጣሙ አዋጆችና ደንቦች ሥራ ላይ አይውሉም።

ተጽፎ ያለው መመሪያ ምንም ይሁን ምን በገጠር ያለው አርሶ አደር ቁራጭ የእርሻ መሬት፣ የግብርና ባለሙያዎች የምክር እገዛ፣ የማዳበሪያና ዘር ግዢ፣ ብድር ወይም እርዳታ ለማግኘት መወየን ይኖርበታል። በከተሞች ውስጥም ሥራ ለመቀጠር፣ ለደረጃ እድገት፣ ለከፍተኛ ትምህርት እድል መወየን አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው:: በንግዱም ዘርፍ የሥራ ቦታ ለማግኘት፣ የመንግሥት ጨረታዎችን ለማሸነፍ፣ የባንክ ብድር ለማግኘት፣ ከጉምሩክ እቃ ለማስለቀቅ፣ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት መወየን ግድ ነው። በገጠር ለልማት ስብሰባ የወጡ አርሶ አደሮች በስብሰባው መጨረሻ የአንዱ ወያኔ ቅርንጫፍ አባል መደረጋቸው ይነገራቸዋል። መምህራንና ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች ለቢ.ፒ.አር ተብለው ይሰበሰቡና ካልወየኑ በስተቀር በአዲሱ አሠራር ቦታ እንደማኖራቸው እንዲያውቁት ይደረጋል። እነ መለስና ስብሃት በእንዲህ ዓይነት መንገድ ያጠራቀሙትን አባል ደማምረው ሰባት ሆነን የጀመርነውን ድርጅት በቅርቡ ሰባት ሚሊዮን እናደርሰዋለን ብለው ይፎክራሉ።

ለምንድነው ወያኔ የአባላቱን ቁጥር ለማብዛት እንዲህ የተንገበገበው? ፍላጎቱ የቁጥር ብዛት ብቻ ከሆነ ለምን የስም ዝርዝር በቀጥታ ከሕዝብ ቆጠራ መዝገብ አይገለብጥም?

አባላትን በግዴታም ሆነ በማባበል መመዝገብ ወዳጆችን ማፍራት ማለት አለመሆኑን የወያኔ መሪዎች ያጡታል ብሎ መገመት የዋህነት ነው። የደርጉ ኢሠፓ እጣ ፈንታ በአይናቸው ያዩት ነገር ነውና የቆሙበት መሠረት ሲናጋ የገነቡት ድርጅት እንደሚፈራርስም የሚያጡት አይመስልም። ታድያ ከዚህ ጅምላ የአባልነት ምልመላ ጀርባ ምን የተደበቀ ሸር አለ? የዚህ ምላሽ በመግቢያው ላይ ባጭሩ ቀርቧል። በመጠኑም ቢሆን ዘርዘር አድርገን እንመልከታቸው::

### 1. ሁሉን ጠቅላይ አገዛዝን ማስፈን

ወያኔ እየገነባው ያለው አገዛዝ ስታሊን ለሠላሳ ዓመታት ሶቭየት ኅብረትን፤ ኤንቨር ሆዣ ለአርባ ዓመታት አልባኒያን ጠፍረው የገዙበት ስልት ነው።

በዚህ የአገዛዝ ስልት መሠረት በፓርቲና መንግሥት መካከል ልዩነት የለም፤ የሁለቱም ዋና ሥራ ዜጎችን መቆጣጠር ነው። ለቁጥጥር እንዲያመች ደግሞ እያንዳንዱ ሰው በመዋቅር መያዝ አለበት። የሚሸመደድ ድጋም እንጂ የሚታሰብ አዲስ ነገር የለውምና የአመለካከትና የርዕዮተዓለም ጉዳይ እጅግም የሚያሳስብ አይደለም። ዋናው መመዘገብና በመዋቅር መታቀፍ ነው።

የወያኔዋ ኢትዮጵያ ሞዴል የኤንቨር ሆዣዋ አልባኒያ ስለመሆኗ በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ቢቻልም አንዱን ብቻ አንስተን እንለፍ። ወያኔ እስከ 2002 ምርጫ ድረስ ስድሳ በመቶ የትግራይ ክልል ነዋሪን አባል የማድረግ እቅድ ነድፏል። የተባለው ጊዜ የተቃረበ በመሆኑ ይሄኔ እቅዱ ሙሉ በሙሉ ተሳክቶ ሊሆን ይችላል። ለምን 60% ተመረጠ? መልሱ 40%ው ነዋሪ ገና “ለአቅመ ፓርቲ” ስላልደረሰ!!! በወያኔ እሳቤ እድሜው የደረሰ ትግራዋይ በሙሉ የወያኔ አባል መሆን አለበት - አለበለዚያ ለነፍጠኞች ያደረ ከሃዲ ነው። ይህ ስዕል የትግራይ ሕዝብ በእንዴት ያለ አፈና ውስጥ እንዳለ ያሳያል። ይህ በትግራይ ላይ ጎልቶ ይታይ እንጂ የመላዋ ኢትዮጵያ ሃቅ ነው። የወያኔ ህልም ሁሉንም ዜጋ በፓርቲ መዋቅር ውስጥ አስገብቶ ጠፍሮ አስሮ መግዛት ነው።

ሕዝብን በድርጅት አባልነት ስም በመዋቅር ማስገባት ለአንባገነኖች የሚሰጠው ዋነኛ ጥቅም የማኅበረሰብን ስነልቦና መስበሩ ነው። ዜጎች የአምባገነኑን መንግሥት ኃይል በመጠን በላይ አግዝፈው፤ የራሳቸውን ደግሞ አንኳሰው እንዲመለከቱ ያደርጋቸዋል። “መንግሥት እያንዳንዱን ነገር አብጠርጥሮ ያውቃል” በሚል የፍራቻ ቆፈን ተይዘው እንኳንስ በተግባር መቃወም ማሰብን እንኳን እንዲፈሩ ያደርጋቸዋል። እያንዳንዱ ሰው ጓደኛውን እንዲጠረጥር በማድረግ የአምባገነኖች የስለላ ተቋም ጠንካራና ሁሉን_አዋቂ እንዲመስል ያደርጉታል።

ሁሉን ጠቅላይ አገዛዝ ወያኔን በእጅጉ ጠቅሞታል። የወያኔ የጦር ሠራዊትና የስለላ ተቋም ደካሞች ናቸው - እነዚህ ሁለቱ ተቋማት እንዳሁን ተዳክመው አያውቁም። የወያኔ ስለላ - ለምሳሌ - በመሃይም ጆሮ ጠቢዎች የተሞላ፤ በቀላሉ የሚታለሉ፤ ዓይናቸው ሥር የሚሠራውን እንኳን ማየት የማይችሉ ድውያን ናቸው። ቀላል ማስረጃ ለመስጠት ዓይኖቻቸውን ባፈጠጡበት ወህኒ ቤት ውስጥ መጽሃፍ ተጽፎበት ሲወጣ፣ ሲታተም፣ ከተማ ሲሸጥ አላዩም፤ አልሰሙም። ብዙ ሰው በወያኔ መዋቅር መያዙ ሕዝብ ልብ ውስጥ የዘራው ፍርሃት እነዚህ ተቋማት የሌላቸውን ግዝፈት ያላቸው እንዲመስል አድርጓል።

### 2. “እንድዘርፍ አግዘኝ፤ አለበዚያ ግን አጠፋሃለሁ”

ስታሊንና ኤንቨር ሆዣ በፋሺስታዊ ጭካኔያቸውና በሁሉን ጠቅላይ አምባነን ሥርዓታቸው የሚጠሉ ቢሆንም ተራ ወንበዴዎች ግን አልነበሩም፤ የአገራቸውና መንግሥታቸው ክብር በማዋረድም አይታሙም። ወያኔ ግን ኢትዮጵያን በመጥላት ያደጉ ግለሰቦች ቡድን ነው። እነዚህ ግለሰቦች ሲዘርፉም ሆነ ሲዋሹ ለከት የላቸውም። ወያኔ የሚያካሂደው መጠነ ሰፊ ዝርፊያ ያለ ብዙ ኢትዮጵያዊያን ትብብር በጥቂት የወያኔ ግንባር ቀደም አባላት ብቻ ሊከናወን ፈጽሞ ባልቻለም ነበር። እናም ለኑሮ ብሎ ወያኔን የተቀላቀለ ከሚከተሉት ቢያንስ በአንዱ መንገድ መተባበሩ አይቀርም።

#### 2.1 በዝርፊያ መተባበር

ኢትዮጵያዊያን ለትናንሽ ጥቅሞች ብለው የወያኔ አባል በሆኑ መጠን ወያኔ የዝርፊያውን አድማስ ያሰፋል። “የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ” የሚሉ ሰዎች መኖራቸው ወያኔን ጠቅሞታል። በትንሹ እንኳን የጥቅም ተካፋይ የሆነ ሰው ትልቁን ዘረፋ የመቃወም ድፍረት ያጣል። በዚህ የተበረታታው የወያኔ ዘረፋ እየሰፋ መጥቶ እነሆ የእርሻ መሬቶችን ለባእዳን እስከ መሸጥ ደርሷል። አንድ ኢትዮጵያዊ በወያኔ አባልነቱ የሚያገኘው ጥቅም ራሱን ለባርነት የሸጠበት ዋጋ አድርጎ ቢያየው ይመረጣል።

#### 2.2 በዝምታ መተባበር

ፍርሃት በፈጠረው የአቅመ ቢስነት ስሜት ወይም ከዚህ በፊት የተደረጉት ጥረቶች ባለመሳካታቸው ሳቢያ የተፈጠረው ደንታ ቢስነት ለወይን-ለመኖር መስፋፋት ተጨማሪ ምክንያቶች ሆነዋል። ቁጥራቸው ጥቂት ያልሆነ ኢትዮጵያዊያን ልባቸው ከግንቦት7 ጋር ቢሆንም ፍርሃታቸው ከወያኔ ጋር አሰልፏቸዋል።

### 3. ፊውዳላዊ መኮፈስ

ግብር ማብላት የኢትዮጵያ ፊውዳል ባህል ነው። ሀዲስ ዓለማየሁ “በፍቅር እስከ መቃብር” በበዛብህ አንደበት እንደተናገሩት የመኳንንት ግብር ግብዣ ሳይሆን ሰው ለቁራጭ እንጀራ ራሱን አዋርዶ፣ ተገፍትሮ፣ ተደብድቦ፣ የማይበላ በልቶ ተገዢነቱን በተግባር የሚገለጽበት፤ መኳንንቱም ይህንን እያዩ የሚደሰቱበት ሥርዓት ነው።

ወያኔ ይህንን የቆየ የፊውዳል ባህል አዲስ ቀለም ሰጥቶታል። የወያኔ አባል በመሆን ለሚገኝ ትንሽ ጥቅም ብዙዎች ክብራቸውን አሳልፈው ሲሰጡ፤ በየግምገማው ስድብን እንደ ምርቃት ሲቀበሉ የወያኔ መኳንንት ሃሴትን ያደርጋሉ፤ “ተራሮችን ስላንቀጠቀጠው” ትግላቸው በየጊዜው አዳዲስ ነገር እየጨማመሩበት ይደሰኩራሉ።

### “ወይን ለመኖርን” ለማጥፋት ምን ማድረግ እንችላለን?

1. ከሁሉ አስቀድሞ ለራሳችን ክብር እንስጥ፤ ለጥቅም ወይም በፍርሃት ምክንያት የወያኔ አባልነት ፎርም በመሙላት ባርነትን አንቀበል።
2. እኛ የምናልማት ኢትዮጵያ ለጥቅም ሲሉ ወይም በፍርሃት ነፃነታቸውን አሳልፈው በሚሰጡ ሰዎች መገንባት አትችልም። እንቢ ለወያኔ ያሉ ወገኖቻችን የተጎናፀፉትንና ወደፊትም የሚኖራቸው ክብር፤ ከማይቀረው የወያኔ ውድቀት በኋላ ተባባሪዎቹ የሚደርስባቸው ውርደት ጋር በማወዳደር ለልባችን ልብ እንስጥ።
3. ከሁሉ አስቀድሞ ማሸነፍ የሚኖርብን በውስጣችን ያለውን ፍርሃት ነው። የወያኔ ሠራዊት ምን ያህል ደካማ እንደሆነ ሶማሊያና ኦጋዴን አሳይተውናል፤ አንበሳ የሚመስለው በሚፈራበት ቦታ ብቻ ነው። የስለላ ተቋሙ ጥቂት ዘረኞች የተሰባሰቡበት የማይማን ጎተራ ነው። አባላቱ አስተሳሰባቸው ትንሽ፤ ብቃታቸው ዝቅተኛ ነው። እነዚህ ኃይሎች ሁሉን ነገር የተቆጣጠሩት አድርጎ ማሰብ ራስን ማዋረድ ነው። ስለዚህም መሸሽ ሳይሆን በየጊዜው ልንፈታተናቸው፣ ልንጎነታትላቸውና ልንፋለማቸው ይገባል።
4. የነጻነት ኃይሎች መዋቅራቸውን ማስፋትና በርካታ ህዋሶችን መፍጠር እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። የወያኔን የመዋቅር ስፋት በነፃነት ኃይሎች የመዋቅር ስፋት መጋፈጥ መቻል አለብን። ህዋሶቻችንን በሁሉም ቦታና ባልተማከለ አደረጃጀት ጭምር በብዛት በመመስረት አገራችን የእኛ መሆኗን ለሕዝባችን ማሳየት አለብን።
5. በማናቸውም ምክንያት ራሳቸውን ወያኔ ጉያ ውስጥ ያገኙ የሕዝብ ወገኖች ካሁን በኋላ መሥራት ያለባቸው ወያኔን ከውስጥ ሆኖ የማፍረስን ሥራ ነው።

“ወይን ለመኖር” የኢትዮጵያን ሕዝብ ያዋረደ፤ ለትውልድ የሚተርፍ የማኅበራዊ ስነልቦና ኪሳራ የሚያደርስ፤ ደካማውን ወያኔን ጠንካራ በማስመሰል የሕዝባችንን የትግል ሃሞት የሚያፈስ በመሆኑ ሁላችንም አጥብቀን ልንዋጋው ይገባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ንጹሃን ዜጎችን አሸባሪዎች በማለት ከሶ የሞት ቅጣት ያስፈረደው አቃቢ ህግ በመተሃራ በተዘጋጀ ድግስ ተሸለመ

የዘረኛውን ወያኔ ኢሃዴግ አገዛዝ ስርአት በሃይል ለመናድ ሲንቀሳቀሱ ደርሼባቸዋለሁ በሚል በሃገር ውስጥ በወያኔ ኢሃዴግ በተደራጀው የመከላከያ ሰራዊት ውስጥ በከፍተኛ ወታደራዊ አመራር ውስጥ የነበሩ እነ ብርጋዴር ጄነራል አሳምነው ጽጌን፣ ከሃገር ውጭ ደግሞ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ አመራር ዶ ር ብርሃኑ ነጋ አንዳርጋቸው ጽጌንና ሌሎች ንጹሃን ኢትዮጵያዊያን በተቀነባበረ የሃሰት ወንጀል ከሞት ቅጣት እስከ እድሜ ልክ እስራት እንዲፈረድ ያደረገው አቃቢ ህግ መርሳ በመተሃራ በተዘጋጀ ድግስ መሸለሙን ዘጋቢያችን ከስፍራው ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በስልጣን ወምበሬ ላይ እንዳልቆይ ያሰጉኛል ያላቸውን ውድ ኢትዮጵያዊያን በፍርድ ቤት ክስ በማቅረብና ጉዳዩንም በተለየ መንገድ በማጣራት እያዘጋጀ የወንጀል ክሱን በባለቤትነት ለመያዝ የፍትህ ሚኒስቴር ልዩ ቡድን አደራጅቶ እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን እንዲህ አይነት የተቀነባበሩ ክሶችም ለአረመኔው ስርአት ዋልታና ማገር ሆነው የሚያገለግሉት ሆድ አደር የህግ ባለሙያዎች የሚያዘጋጁትን የወንጀል ክስ ለሃሰተኛው ፍርድ ቤት አቅርቦ የሚያስቀጣ አቃቤ ህግም ተደረጅቶ እንደነበር ይታወሳል።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት አቃቤ ህግ መረሳ የሚባል ከትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ በልዩ ትእዛዝ ተመልምሎ አዲስ አበባ ፍትህ ሚኒስቴር እንዲቀላቀል ተደርጎ እንደነበር፣ የታወቀ ሲሆን ይሄው አቃቤ ህግ በሃሰትና ሙሉ በሙሉ በፈጠራ የተዘጋጀውን ይህንን መሰል ጉዳይ ለመከታተል ለተዋቀረው የዘረኛው አገዛዝ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልዩ ወንጀል ችሎት አቅርቦ ዳኞቹ የአቃቢ ህጉን ሚና ተከተው በተወኑት ድራማ ተጠርጣሪዎች ጥፋተኛ ናቸው ተብለው በሞት፣ በእድሜ ልክ፣ እስራትና በተለያየ ኣመታት እስራት እንዲቀጡ፣ የድራማው ዋና ተዋናይ በመሆን አገልግሉአል።

ሽብርተኛ ናችሁ የተባሉትን ዜጎች ክስ ወደ ፍርድ ቤት አቅርቦ፣ ችሎት ላይ ቆሞ የክርክሩን ሂደት ሲመራ የነበረው አቃቤ ህግ መረሳ፣ ሽብርተኝነትን በወንጀል ፍርድ ቤት አቅርበው ያስፈረዱ አቃቤ ህግ ተብሎ በመተሃራው ድግስ ተወደሰ፣ በስሙም ኮከብ አቃቤ ህግ መሆኑን የሚገልጽ የምስክር ወረቀትና ሜዳሊያ ተበረከተለት።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት አቃቤ ህግ መርሳን ለመሸለም፣ ክብረ በአል ከአዲስ አበባ ውጪ በመተሃራ ከተማ ተዘጋጅቶና፣ ሚንስትሩን ጨምሮ የመስሪያ ቤቱ ከፍተኛ ባለስልጣናትና አመራሮች በተገኙበት ለአቃቤ ህግ መርሳ ይህ ሽልማት ሲበረከትለት አቃቤ ህግ መረሳ በምስክር ወረቀቱ ላይ የሰፈረውን ቃል ሲመለከት በመደሰት ፋንታ፣ እጅግ እንደተበሳጨ ታውቋአል።

አቃቤ ህግ መረሳ የምስክር ወረቀቱንና ሜዳሊያውን እንደተቀበለ ወዲያው፣ ተመናጭቆና አንገቱ ላይ ያጠለቀውን መዳሊያ አውልቆ እያወናጨፈ፣ ቀድሞ ተቀምጦበት ወደነበረው ቦታ ሄዶ፣ ሲቀመጥ ፣ አጠገቡ የነበረው አቃቤ ህግ ሹም ለምን መረሳ እንደተቆጣ የጠየቀው ሲሆን፣ አቃቤ ህግ መረሳም እየው በምስክር ወረቀቱ ላይ የሰፈረውን፣ እነ ዶ ር ብርሃኑ ነጋ የሚባሉ አሸባሪዎች ላይ ተከራክሮ የሞት ቅጣት በማስፈረዱ የሚል ነው፣ የተጻፈው፣ ይህ ደግሞ ነገ እንደማስረጃ ሆኖ እኔኑ የሚያሰቅለኝ ነው ብሎ መናገሩ ታውቋአል።

ዘጋቢያችን አቃቤ ህግ መረሳ የተበሳጨበትን ምክንያት በሚመለከት አስተያየት እንዲሰጡት የጠየቃቸውና በመተሃራ ከተማ ድግስ ላይ የተገኙ የፍትህ ሚኒስቴር ባልደረባ እንደተናገሩት መረሳ ህሊናውን የሚቃረን ወንጀል እንደሚሰራና ይህም ነገ ጠዋት ለህዝብ ፍርድ እንድሚያበቃው አንጠርጥሮ የሚያውቅ መሆኑን መረዳት ይቻላል። በጣም የሚገርመው ደግሞ ይህ አገዛዝ እድሜው አጭር መሆኑን መገንዘቡና፣ ነገ ጡአት ሊከሰትበት የሚችለውን ፍርድ በጊዜ ረዳቱ ነው በማለት መልሰዋል።

## በጀርመን አገር በኑረንበርግ ከተማ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ወያኔ በህዝቦች መከፋፈል የሥልጣን ዕድሜውን በማራዘም ላለፉት 20 አመታት የሁሉንም ህዝብ ስቆቃ በማባባስ ላይ ይገኛል ያሉት አቶ ተማም ባቲ ፤ ይህ የወያኔ አገዛዝ ሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በሕዝብ ላይ ያደረሳቸውን እና እያደረሰ ያሉትን ችግሮች በአሁኑም ሰዓት የፈጠረውን የኑሮ ውድነት እና የዋጋ ግሽበት የህዝባችንን ስቃይ ከምንጊዜውም የከፋ አድርጎታል ካሉ ቦኋላ የዚህን ሥርዓት ዕድሜ ለማሳጠር ድርጅታቸው አነግ ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ከሚታገሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር በጽናት ለመታገልና ትብብር ለመፍጠር የሚያስችለውን አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት መጨረሱን ይፋ አድርገዋል።

በድርጅቶች መካከል የሚደረጉ የመቀራረብ ሥራዎች ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ ምን ያህል አስፈሪና አስደንጋጭ እንደሆነ ተቀራርበን ለመነጋገር የጀመርነውን ፓርቲዎች ማለትም ግንቦት 7፤ የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባርና ድርጅታችን አነግን በቅርቡ በአሸባሪነት መፈረጁ ጉልህ ማስረጃ ነው ያሉት የአነግ ሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ አባል፤ ወያኔን ያስደነገጠውን ንግግር ወደ ህብረት በማሸጋገር በጋራ ተንቀሳቅሰን ወያኔን በማስወገድ ህዝብ በመረጠው መንግሥት የሚተዳደርበትን ሥርዓት መፍጠር ከሁላችንም የሚጠበቅ ነው ብለዋል።

ከአነግ አመራር አባል ከአቶ ተማም ባቲ ቀጥሎ ለስብሰባው ንግግር ያደረጉት የግንቦት 7 ሊ./መንበር ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ሲሆኑ በቅርቡ በአሜሪካን አገር አርሊንግተን ላይ የኢትዮጵያ አንድነት አስመልክቶ ተናግረውት የነበረው ቀጣይ ክፍል መሆኑን በማሳሰብ ፤ የኢትዮጵያ አንድነት ጠንካራ መሰረት ላይ እንዲቆም ለማስቻል ፍትህ፤ እኩልነትና ነጻነትን መሠረት ያደረገ የግለሰብ ነጻነት የሚያስጠብቅ ሥርዓት እንዲፈጠር በጋራ መታገል ያለውን ጠቀሜታ አውስተው ለቋንቋ ፤ ለሃይማኖትና ለባህል መብቶቻችንን መከበር በተናጠል የምናካሄደው ትግል አንድነታችንን በመናድ ከፋፍሎ ሊገዙን ለተሰለፉት አምባገነኖች እንድንመቻች ያደርገናል የሚል ስጋት እንዳላቸው ገልጸዋል።

ዶር ብርሃኑ ንግግራቸውን በመቀጠል "በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከስልሳዎቹ ጀምሮ የብሄር ጥያቄን ያስነሳው ዋነኛ ነገር ባህላችን አልተከበረልንም የሚል ጥያቄ መሆኑን በማውሳት ባህል ለአንድነታችን ምክንያት ሊሆን እንደሚችለው ሁሉ ለመለያየታችን እና አከራካሪ ጥያቄን ለማንሳት መነሻ ሊሆን እንደሚችል አብራርተዋል። ታሪክም እንዲሁ እንደባህል ሁላችንንም ሊያስማማ እንደማይችል በመጥቀስ መሰረታችን ሊሆን የሚገባው የፍትህ እና የዜግነት እኩልነት መሆኑን ያስረዱት የግንቦት 7 ሊቀመንበር የሕግ የበላይነት የሌለበት አገር ውስጥ የባህል የቋንቋ እና ሌሎች አንድ ያደርጉናል የምንላቸው ነገሮች ለልዩነት መምጣት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ ብለው እንደሚሰጉ የሌሎችን አገሮች ልምድ በመዘርዘር አስረድተዋል።

በቋንቋ ላይ ብቻ መሰረት ያደረጉ ማንነቶች ከኢትዮጵያ በመገንጠል መፍትሄ ሊያገኙ አይችሉም ሲሉ በአጽንዖት የገለጹት ዶ/ር ብርሀኑ፣ የማንኛችንንም አንድነት የሚያጠናክረው ዋንኛው ነገር በፍትህ እና በፖለቲካ እኩልነት ላይ መሰረት ያደረገ አንድነት መሆኑ ከሚያራርቁን ነገሮች በላይ የሚያቀራርቡን እሴቶች መሆናቸውን በማውሳት በሚያቀራርቡን ነገሮች ላይ ጠንክረን ከሠራን ኢትዮጵያዊነትን ያለ ችግር ማምጣት እንደምንችል ገልጸዋል።

ዶ/ር ብርሀኑ ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ በዘውግ የተደራጁ ድርጅቶች በተለይ ኦሮሞዎች የትግሉ መሪ መሆን መቻል እንዳለባቸውና ይህንንም ኃላፊነት በመሪነት እስካልተወጡ ድረስ ሁሌም በነሱ ላይ ጥርጣሬ እንደሚኖር አስታውሰው፣ ሌሎች ድርጅቶች ስሜት ለማነሳሳት እና ድጋፍ ለመሰብሰብ ብቻ ሲባሉ የሚደረጉ ጽንፈኝነትን የሚፈጥሩ ኃላፊነት የጎደላቸው ጥሪዎች እና ቅስቀሳዎች መቆም መቻል እንዳለባቸው መክረዋል።

ከሁለቱ ንግግር ቦኋላ በስብሰባው ላይ የተገኙት ተሰብሳቢዎች የተለያዩ ጥያቄዎች አቅርበው ምላሽ ያገኙ ሲሆን በተለይ የኦሮሞ ኮሚኒቲ አባላትና የአነግ ደጋፊ የሆኑ ተሰብሳቢዎች በኦሮሞ ብሄርተኝነት ዙሪያ ሲጠነጠን የነበሩ የመብት ጥያቄዎችን አንድ በአንድ ለመጠየቅ እንደቻሉና ከመድረኩ በተሰጣቸው ምላሽ እንደተደሰቱ ዘጋቢያችን አክሎ ዘግቧል።

## ጥምረት ለነጻነትና ለእኩልነት ከኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ጥምረትን በመወከል በዚህ በሎንዶኑ ስብሰባ ላይ ንግግር ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቅ የነበሩት የአፋር ህዝቦች ፓርቲ የውጪ ግንኙነትና የፋይናንስ ሃላፊ ዶር ኮንቴ ሙሳ በአካል ለመገኘት ሳይችሉ ስለቀሩ በቪዲኦ ኮንፍረንስ ንግግር በማድረግ ኮሌኔል መሃመድ የተባሉ የድርጅቱ አመራር አባል እንዲተኩዋቸው ያደረጉ ሲሆን ግንቦት 7ን በመወከል የንቅናቄው ዋና ጸሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ በየተራ ንግግር አድርገዋል።

የሁለቱም ንግግር ያተኮረው በወቅቱ ያገራችን ፖለቲካ አንዳንድ ፓርቲዎች የሚያነሱዋቸው የታሪክ ክርክሮች መሠረት ያደረጉና ማናችንንም ሊያግባባ በማይችል አከራካሪ የታሪክ ክርክሮች ውስጥ ሆነን ለወያኔ ሥልጣን ዕድሜ መራዘም አስተዋጽኦ ከምናደርግ፤ ፍትህ እኩልነትና ነጻነት የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በአገራችን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት በጋራ ታግለን ታሪክ ጥሎብን ያለፈውን ጠባሳ ለማሻር መሥራት እንደምኖርብን ጥሪ የሚያደርግና በዕለቱ ስብሰባ ላይ የተገኙት ፓርቲዎች ስለ ጋራ ትብብር አስፈላጊነት በቂ ግንዛቤ በመፍጠር ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ መጀመራቸውን የሚያመላክት ነበር።

## አረመኔው የወያኔ አገዛዝ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አስተያየት ይህ አገዛዝ መቼም ተወርቶ የማያልቅ ግፍና በደል በኢትዮጵያዊያን ላይ እየፈጸመ መሆኑ ሁላችንም የምናውቀው ነው።አሁንም ምንም ህዝብ አልተራበም፣ ችግሩ የድርቅ ችግር ነው በማለት ቃል ምልልስ የሚያደርገውም እዚህ ሃገር ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ ምንም አይነት አማራጭ መረጃ አያገኝም በሚል እንደሆነ ገልጸው፣ አገዛዙ ይህን ያስብ እንጂ እኛ ከተለያዩ የዜና አውታሮች አይደለም በሃገራችን በሌሎች ሃገራትም እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ እናውቃለን፤ እናም ለሚኒስትር ዴታ ተብየው ቃለ ምልልስ ዋጋ የሚሰጥ ኢይትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም ብለዋል።

በ60 አመት ታሪክ ዉስጥ በአፍሪቃ ቀንድ ታይቶ የማይታወቀዉ የረሃብ አደጋ 11.5 ሚሊዮን በሚሆን ህዝብ ህይወት ላይ ያንዣበበዉን አሳሳቢ የሞት አደጋ ለማስቀረት አለም አቀፍ የረድኤት ድርጅቶች በሚረባረቡበት ወቅት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት ረሃብተኞች እንዳይታዩ አሁንም የመረጃ አውታሮች ባካባቢው እንዳይንቀሳቀሱ እንደከለከለ ሲሆን፤ የረሃብተኞችን ቁጥር በትክክል ይፋ አለማድረጉም መዘገቡ ይታወሳል።

## ሱዳን ውስጥ አቢየ ላይ የሰፈረው የኢትዮጵያ ጦር ሃይል አጣብቂኝ ውስጥ ወደቀ

የደቡብና ሰሜን ሱዳንን ለሁለት መከፈል ተከትሎ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አማካኝነት ሱዳን ውስጥ የአቢየን ተልእኮ እፈጽማለሁ በማለት ለዳግማዊ ጦርነት የሰፈረው የኢትዮጵያ ጦር የሚንቀሳቀሰውና የሚመራው በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አማካኝነት ከሆነ ድርጊቱን ሰሜን ሱዳን እንደማትቀበለው መግለጹዋን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ባወጣው ዘገባው ላይ አመልክቱአል።

እንደ ኢሳት ዘገባ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በአቢየ እንዲሰማራ የማትፈልገው ሰሜን ሱዳን፣ የኢትዮጵያ ጦር እንቅስቃሴ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ትእዛዝ ስር የሚሆን ከሆነ ቀደም ብሎ የገባችዉን ስምምነት እንደምታፈርስ መግለጹአ ታውቁአል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሱዳን ውስጥ የሰፈረውን የኢትዮጵያ ጦር መምራት የማይፈቀድለት ከሆነ የኢትዮጵያን ጦር ወጪ ለመሸፈን ባለመቻሉ ድርጅቱ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገባል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ቀደም ብሎ በሶማሊያ ለተመሳሳይ ተልእኮ በሺሆች የሚቆጠሩ ወታደሮችን አስፍሮ እንደነበርና፣ ጦሩም በደረሰበት ሽንፈት ወደመጣበት እንዲመለስ የተደረገ መሆኑ በሰፋት የተዘገበ ሲሆን፣ የአሁኑ የሱዳን ውውስጥ ተልእኮ ገና ከጅምሩ እንዲህ አይነት አጣብቂኝ ውስጥ መውደቁ በርካቶችን እያነጋገረ እ ይገኛል።

ባለፈው ወር በኢትዮጵያ ጦር ሃይል መኮንኖች ላይ ድንገተኛ ጥቃት መፈጸሙን ቀደም ብለን መዘገባችን አይዘነጋም።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ፡-** በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ፡-** በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz
እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:00 እስከ 2:30 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን። **ማሳሰቢያ፡-** ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org